# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 180 ጥቅምት 16 2004 ገጽ 1

ግንቦት 7፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ሊቢያ ላይ እንደረሰው ዓይነት የህይወትና የንብረት መስዋዕትነት ሳይከፈል የሥርዓት ለውጥ ማምጣት ይቻላል ብሎ ያምናል። ለዚህ ግን የመለስ ዜናዊና ዘረኛ ቡድኑን ፈቃደኝነት ይጠይቃል። ስለሆነም በመለስ ዜናዊ ዙርያ ያላችሁ ሁሉ ወደ ልቦናችሁ ተመለሱ እንላለን። እብሪት የትም እንደማያደርስ ከጋዳፊ አይተነዋል።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## ግንቦት 7 በአውሮጳ ከሚገኙ የየአገራቱ አመራር አባላት ጋር ያካሄደው የሁለት ቀን ስብሰባ በተሳካ ሁኔታ መፈጸሙ ተገለጸ

በአውሮፓ ከሚገኙ 11 አገሮች የተወጣጡ የግንቦት 7 የአህጉርና የአገራት ተወካዮች ባለፈው ቅዳሜና እሁድ እንደፈረንጆች አቆጣጠር ኦክቶበር 22 እና 23 ከአውሮጳ ዋና ከተማ ከብራስልስ 30 ኪ.ሜትር ርቆት ላይ በሚትገኘው የሉቨን ከተማ ተሰባስበው ንቅናቄያቸው ስለሚያካሄደው ሁለገብ ትግል በሰፊው እንደተወያዩና የአቋም መግለጫም እንዳወጡ የንቅናቄው የህዝብ ግንኙነት ክፍል አስታወቀ።

ከስዊድን፤ ከኖርዌዩ፤ ከዴንማርክ፤ ከፊንላንድ፤ ከሲውዘርላንድ፤ ከኢስፔን፤ ከፈረንሳይ፤ ከጀርመን ከእንግሊዝ፤ ከኔዘርላንድስና ከቤልጅዬም የተውጣጡት እነዚህ ተሰብሳቢዎች፤ በየአገሩ በተዘረጋው የግንቦት 7 ድርጅታዊ መዋቅር ውስጥ በሥራ አመራር ኮሚቴ ተመርጠው ትግሉን እያሰተባበሩ ያሉ መሆናቸው ታውቆአል።

በሰሜን አፍሪካ ውስጥ በተቀሰቀሰው የጸረ አምባገነኖች ትግል የተደናገጠው የመለስ ዜናዊ ፋሽስታዊ አገዛዝ፤ ለሁለት አሥርቴ አመታት በህዝባችንና በአገራችን ላይ እየፈጸመ ያለውን ሰቆቃና ወንጀል ይበልጥ በማጠናከር ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ስላማዊ ዜጎችን፤ ጋዜጠኞችን፤ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ መሪዎችንና አባላቶቹን በሽብርተኝነት ሥም እየፈረጀ፤ እራሱ ከሳሽ እራሱ ዳኛና ምስክር በመሆን ምን ያህል እያሰቃዩ እንደሚገኝ በሰፊው የተወያየው ስብሰባ፤ ንቅናቄያቸው ግንቦት 7 ይህንን የወያኔን እብሪት ለማስቆም በምድር ላይ ምን እየሰራ እንደሆነ በንቅናቄው ሊቀመንበር በዶ/ር ብርሃኑ ነጋ አማካይነት ሰፊ ማብራሪያ እንደተሰጠው ለማወቅ ተችሎአል።

ከድርጅቱ ሊቀመንበር ከዶር ብርሃኑ ነጋ በተጨማሪ የንቅናቄው የተለያየ ዘርፍ ሃላፊዎች ተገኝተው ከአባላቱ ለተነሱት የተለያዩ ጥያቄዎች ምላሽ የሰጡ ሲሆን እየተሰራ ነው በተባለው ድርጅታዊ ሥራ እርካታ የተሰማቸው የየአገሩ አመራር አባላት፤ ንቅናቄው በምድር ላይ እያከናወነ ያለውን ሁለገብ ትግል በሚያስፈልገው ሁሉ ለመደገፍ ከምንጊዜውም በላይ ቆርጠው መነሳታቸውንና ወደየመጡበት አገሮች ሲመለሱም በስብሰባው ላይ ለመሳተፍ ዕድል ያላገኙትን መላውን አባላትና ደጋፊዎች በማነቃቃት ለትግሉ እጅግ አስፈላጊ የሆነውን የገንዘብ፤ የማቴሪያልና የእውቀት ድጋፍ እንደሚያስባስቡ በማረጋገጥ ባለ 4 ነጥብ የአቋም መግለጫ በማውጣት ስብሰባቸውን እንዳጠናቀቁ ታውቆአል።

## የፋሽስቱ መለስ ዜናዊ ውድቀት እንደሊቢያው ሙአመር ጋዳፊ እንዳይሆን ስጋት መኖሩን የህዝብ አስተያየት አመለከተ

ተቃዋሚዎቻቸውን አንዴ ሽብርተኞች፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ በሃሺሺ የደነዘዙ አይጦች በማለት ሲያጣጥሉ የነበሩትን የሙአመር ጋዳፊ የውርደት አሟሟት የተመለከቱ በርካታ ኢዮጵያዊያን የመለስ ዜናዊ የመጨረሻ እጣ ፋንታ ተመሳሳይ ሊሆን እንደሚችል በስፋት እየተነበዩ መሆኑን በአዲስ አበባና አጎራባች ከተሞች የሚኖሩትን የህዝብ አስተያየት ያሰባሰቡ የግንቦት 7 ዘጋቢዎች ለዝግጅት ክፍላችን በላኩት ዜና ገለጹ።

ሙአመር ጋዳፊ በዙሪያቸው ያደራጁትን የመከላኪያ ሠራዊት ብዛትና ጥንካሬ በመተማመን በተቃዋሚዎቻቸው ላይ ሲሰነዝሩ የኖሩት ንቀትና ጥላቻ መለስ ዜናዊ ወደሥልጣን ከመጣ ጊዜ ጀምሮ ከሚያሳየው ይመሳሰላል ያሉት አሰተያየት ሰጪዎች ፤የሊቢያው ጦር ሙአመር ጋዳፊና ልጆቻቸው የተጎነጩትን አይነት ውርደት ሊያስቀር እንዳልቻሉ ሁሉ መለስ ዜናዊ የተመካበት ሠራዊት ፊቱን ወደ ህዝብ ዞር ያደረገ ቀን ፍጻሜው ተመሳሳይ እንደሚሆን ፍጹም አንጠራጠርም ይላሉ።

ዘጋቢዎቻችን ካሰባሰባቸው የህዝብ አስተያየቶች አንዱ የሆኑት የደቡብ ዩኒቨርሲቲ መምህር ፤ በሰጡት አስተያየት እንደተናገሩት፣ ምንም እንኳን በአለም ላይ ያሉ አምባገነኖች ካንድ ውሃ የተቀዱ ቢመስሉንምና አንደኛው ከሌላው መማር አለመቻሉ አዲስ ነገር ባይሆንም፣ አሁን በሙአመር ጋዳፊ ላይ የደረሰው ውድቀትና የሊቢያዊያንም እልህ አስጨራሽ ትግል በተለይም ለአምባገነኑ መለስ ዜናዊና በዙሪያው ለተሰባሰቡ የህወሃት ቁንጮዎች ምናልባት የመጨረሻ እድል ሊሆን ይችል ይሆናል ብለው እንደሚያስቡ ገልጸዋል።

በጉልበትና ወታደራዊ ሃይል አጥብቆ መመካት፣ እንዲሁም በዘመድ አዝማድ ላይ የተመሰረተ የስልጣን ክፍፍል መጨረሻው ምን ሊሆን እንደሚችል ሰሞኑን በሊቢያ ያየነው ክስተት ግልጽ ትምህርት (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

## “የምክር ቤት አባልነቴ፤ በቴሌቪዥን ቢሆንልኝ ይሻል ነበር” ሲሉ የኢትዮጵያው አሻንጉሊት ፓርላማ ብቸኛው የተቃዋሚ ፓርቲ ወኪል መናገራቸው ተዘገበ

ሰሞኑን አምባገነኑ መለስ ለአሻንጉሊቱ የኢትዮጵያ ፓርላማ ሪፖርት ባቀረበበት ወቅት ብቸኛው የተቃዋሚ ፓርቲ ተወካይ አቶ ግርማ ሰይፉ ፤ ከወትሮው በተለየ መልኩ በዘረኛው መለስ አስተያዬት ዙሪያ ሀሳባቸውን ለመስጠት እንዳልተፈቀደላቸው መጥቀሳቸውን የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት ዘገበ።

“ይህ ነገር መታረም ካልቻለ ምናልባትም ለምክር ቤቱ ጥያቄዎቻችንን አስገብተን መለስ መልስ እንዲሰጥና እኛም ሂደቱን በቴሌቪዥን ብንከታተል የሚሻል ይመስለኛል” ያሉት አቶ ግርማ፤ “የምክር ቤት አባል መሆኔ ትርጉም የሚኖረው፤በተሰጡት አስተያዬቶች ላይ ሀሳቤን በማንጸባረቅ ስችል ይመስለኛል”ማለታቸውን ተያይዞ የወጣው ዘገባ አመልክቱአል።

እንደ ኢሳት ዘገባ አቶ ግርማ አክለው በተደጋጋሚ አምባገነኑ መለስ በተሳሳተ የመነሻ ምክንያት ተንደርድሮ ያሻውን ዓይነት ድምዳሜ ላይ ሲደርስ ‘ሃይ!’ ለማለት እንኳን አልተቻለም።‘የለም! አንተ ያልከውና እኛ የገባን ይለያያል’ ለማለት እንኳ፤ እድሉን አላገኘንም። ሁኔታው እጅግ አሳፋሪ ነው። የም/ቤት አባልነቴ በቴሌቪዥን ቢሆንልኝ ይሻል ነበር’ ሲሉ መናገራቸው ተገልጹአል።

“ፋሽስቱ መለስ በጋዜጠኞች ላይ የሰነዘራቸውን ትችቶች እንዴት ይመለከቱታል?” ተብለው የተጠየቁት አቶ ግርማ መለስ ከተሳሳተ መነሻ-ምክንያት ተነስቶ ወደ አደገኛ ድምዳሜ የሚሄድበትን አግባብ የሚያሳይ ሌላኛው ጉዳይ ነው” ያሉ ሲሆን “ መለስን ያበሳጨው፤ ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ ብያኔ ከመስጠቱ በፊት ‹የግል ጋዜጠኞች ተከሳሾቹን ነፃ ናቸው ይላሉ› የሚለው ነው” ያሉት ብቸኛው የተቃዋሚ ዕጩ፤ ሰዎች በፍ/ቤት ወንጀለኞች መሆናቸው ተረጋግጦ ወንጀለኛ እስከሚባሉ ጊዜ ድረስ ነፃ መሆናቸው የተረጋገጠ ከመሆኑ አንፃር፤ ይሄ አባባል በሕግ ፅንሰ-ሃሳብም ሆነ ተግባራዊ አሰራር የሚደገፍ እንጂ የሚያበሳጭ እንዳልሆነ አስረድተዋል። (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## በሃዲያ ዞን የሚገኙ የሶስት ወረዳ ህዝቦች ለጥያቄአቸው ምላሽ ካላገኙ አመጽ እንደሚያስነሱ መግለጻቸው ታወቀ

ኢትዮጵያን በዘርና አሃይማኖት ከፋፍሉ የመግዛት አባዜ የተጠናወተው የወያኔ አገዛዝ የከፋፋይነት መርዙን በሃገሪቱ ከረጨ ወዲህ በበርካታ የኢትዮጵያ ክልሎች ግጭቶች እየተከሰቱ ሲሆን ላለፉት 13 ዓመታት "እኛ ሃላባዎች እንጂ ሃድያዎች አይደለንም፤" በሚል የማንነት ጥያቄ ሲያነሱ የቆዩ ናቸው የተባሉ በሃዲያ ዞን ውስጥ የሚገኙ ሦስት ወረዳዎች፣ ጥያቄያቸው ምላሽ በማጣቱ ወደ ግጭት በማምራት ላይ መሆናቸው ታወቀ።

ቁጥራቸው አሥር የሚደርሱ በሃዲያ ዞን ምሥራቅ ባዳዋቾ ወረዳ የአንደኛ ቁራንሶ፣ የሁለተኛ ቁራንሶና የገገራ ቀበሌ ነዋሪዎች ተወካይ ሽማግሌዎች ለዘረኛው አገዛዝ ቅርበት እንዳለው ለሚታወቀው ሪፖርተር ጋዜጣ እንደገለጹት፣ ለ13 ዓመታት የማንነት ጥይቄያቸውን ለወረዳው፣ ለዞኑ እንዲሁም ለደቡብ ክልል ከዚያም አልፎ ተርፎ ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ቢያቀርቡም ምላሽ ከማጣታቸውም ባሻገር ወደ ግጭት እያመሩ ነው።

ባህላቸው፣ ታሪካቸውና ቋንቋቸው የሃላባ መሆኑን የሚናገሩት እነዚሁ ሽማግሌዎች፣ "እውነታው ይህ ሆኖ እያለ የምንማረው፣ የምንዳኘው እንዲሁም ማንኛውንም ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ግንኙነታችንን የምናደርገው በምንም መልኩ መናገር፣ መስማትና ማንበብ በማንችለው የሃዲይኛ ቋንቋ ነው፤" በማለት እየተናገሩ እንደሆነ ታውቁአል።

ጥር 20 ቀን 2000 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ለክልሉ መንግሥት የላከው ደብዳቤ እንደሚያመለክተው፣ የሦስቱ ቀበሌ ነዋሪዎች በሃዲያ ዞን የምሥራቅ ወረዳ አመራር አባላት ለጥያቄያቸው ምላሽ ከመስጠት ይልቅ በተወካዮቻቸው ላይ ድብደባና አፈና እያደረሱባቸው መሆኑን፣ ከዚህም ለማምለጥ አካባቢውን ለቅቀው በስደት እንደሚገኙና የማንነት ጥያቄውን ባቀረቡ ተወካዮች ቤተሰቦች ላይ እስራት እንደሚፈጸምባቸው ተወካዮቹ በአቤቱታቸው ማቅረባቸውን ጋዜጣው ዘግቧል።

የማንነት ጥያቄ መነሳት ከጀመረበት ከ13 ዓመታት ወዲህ በብሔረሰቡ ላይ እየደረሰ ያለው ስቃይ ከልክ በላይ መሆኑን የሚናገሩት ተወካዮቹ፣ ዞኑ ለችግሩ መፍትሔ ከማቅረብ ይልቅ ቅድመ ሁኔታዎችን በመደርደር እየበደላቸው መሆኑን መግለጻቸው ታውቁአል፡፡ የማንነት ጥያቄ የሚያነሱትን በጅምላ በማሰር፣ በመደብደብና ባልሠሩት ወንጀል በማስፈረድ ተደጋጋሚ እንግልት እንደሚያደርሱባቸው የሚናገሩት ተወካዮቹ፣ በተለይ መስከረም 21 ቀን 2000 ዓ.ም. "ሕገወጥ ስብሰባ አካሂዳችኋል፤" በሚል ወረዳው ባሰማራቸው የፖሊስ ኃይል የደረሰው ጥቃት ችግሩን አስከፊ እንዳደረገው አብራርተዋል፡፡ (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## ከጋዳፊ ውድቀት መለስ ይማር!

ሊቢያን ለአርባ ሁለት ዓመታት ቀጥቅጠው የገዙት ኮሎኔል ጋዳፊ በትውልድ መንደራቸው ስርት ውስጥ እጎርፍ ማስወገጃ ቱቦ ውስጥ ተገኙ። እንደተባለው ከሆነ ከወርቅ የተሠራ ሽጉጣቸውን የመጠጣት እድል እንኳን ሳያገኙ በአልባሌ ጥይት ቆሰሉ። “አይጦች:: በረሮዎች ሃሽሻሞች” ዱርየዎች እያሉ በሰደቧቸው እና የመድፍ ናዳ ሲያወርዱባቸው በነበሩ ወጣት አብዮተኞች ጫማ ተረገጡ፣ ተጎሸሙ። በጥፊ ተመቱ፤ ተዋረዱ። በመኪናም ታስረው ተጎተቱ:: እየጮሁ በአሳዛኝና በአዋራጅ ሁኔታ ህይወታቸው አለፈ። ... እጅግ አሳዛኝና አዋራጅ የሆነ አጨራረስ!!!

ጋዳፊ ስልጣንና ከስልጣን የሚገኝን ጥቅማ ጥቅም በዘመድ አዝማድ በማከፋፈላቸው በእሳቸው ላይ የተነሳው ተቃውሞ ጦስም ለመላው ቤተ-ዘመዶቻቸው ደርሷል። በአሁኑ ሰዓት የቤተዘመዶቻቸው አባላት አንድም ተገድለዋል፤ አልያም ተሰደዋል።

የተባበሩት መንግሥታት እና አምነስቲ ኢንተርናሽናል የጋዳፊ አሟሟት እንዲመረመር በመፈለጋቸው የእስልምና ሃይማኖት በሚጠይቀው መሠረት በሞቱ ሃያ አራት ሰዓት ውስጥ አልተቀበሩም። ይህም ለቀሪ ቤተሰቦቻቸው ሌላ ሞት ነው።

“ይወደኛል!!! ህይወቱንም ለኔ ሲል አሳልፎ ይሰጣል!!!” ያሉት ህዝብ ግን በጭፈራ ላይ ነው። የጋዳፊ አስከሬን በአልባሌ ምንጣፍ ላይ ተዘርሮ ለሥጋ ማቆያነት ይውል በነበረ የብረት ሣጥን (ኮንተይነር) ውስጥ ለቀናት ተቀምጦ ለእይታ በቅቶአል። በአገዛዝ ዘመናቸው በአካል ቀርበው ሊያዩዋቸው ያልበቁ ሁሉ አስከሬናቸውን በገዛ ዓይኖቻቸው ለማየት ወረፋ ይዘው ታይተዋል። ይህ ወረፋ የተያዘው በሌላ ሃገሮች እንደሚደረገው ለተከበሩ መሪዎች የመጨረሻውን ክብር ለመክፈል የተያዘ ወረፋ አይደለም። የጋዳፊን በውርደት የተሞላ አፈጻጸም ለመመልከት እንጂ። እንዲያውም የጋዳፊን አስከሬን በማየት ለመደሰት ሲሉ ብዙ መቶ ኪሎ ሜትሮችን ተጉዘው የመጡ ሰዎችም ነበሩ ተብሏል። የሚስራታ ነዋሪዎች የጋዳፊን አስከሬን በማየት ቢደሰቱም በከተማቸው ውስጥ እንዲቀበሩ ግን አልፈቀዱም።

በሌላው ዓለምም ያለው ስሜት ተመሳሳይ ነው። ምናልባት ብዙዎች ጋዳፊ ህግ ፊት ቀርበው ቢያዩዋቸው ይመርጡ ነበር ይሆናል። ያም ሆኖ በመሞታቸው አልተከፋም። ዓለም ከተንሰራፋባት አምባነነኖች አንድ ቀንሶላታልና በጋዳፊ ሞት ተደስታለች።

የዛሬ አንድ ዓመት ሊቢያ ውስጥ የነበረው ሁኔታ ዛሬ ካለው ጋር ማስተያየት እንደምን ያለ ከባድ ነገር ነው!? የዛሬ ዓመት ጋዳፊ ሊቢያን ብቻ ሳይሆን መላውን አፍሪቃ እና መካከለኛውን ምሥራቅ የሚያርበደብዱ ብርቱ ሰው ነበሩ። የዛሬ ዓመት ሁሉ በእጃቸው፤ ሁሉ እደጃቸው ነበር። ለስብሰባው አንዱ አገር ጎራ ሲሉ ዓይኖቻቸው እሳት የሚተፉ በሚመስሉ ሆኖም ግን ቀነጃጅት በሆኑ አጃቢዎቻቸው መሃል እንደ አንባሳ ደቦል ይንጎማለሉ ነበር። የዛሬ ዓመት እንኳንስ በአካል ፊት ለፊት፤ በቴሌቪዥን እንኳን ምስላቸውን ማየት የሚያስፈራ ነበር። የዛሬ ዓመትና ከዚያ በፊት በነበሩ አርባ ዓመታት ሁሉ የጋዳፊ ቃል የፈጣሪ ቃል ያህል ነበር።

ዛሬ ግን ያ ሁሉ ተቀይሯል። ጋዳፊ በተለይ በሊቢያውያን የተናቁ፣ የተዋረዱ፣ የተጠሉ ሰው መሆናቸው ተረጋግጦአል። በአርባ ሁለት ዓመታት ጊዜ ውስጥ “ገነባሁት” ብለው ይኮሩባቸው ከነበሩ ነገሮች ውስጥ እሳቸውን ተከትሎ ለሚመጣው ትውልድ፣ ህዝብና መንግሥት የሚተላለፍ ነገር የለም። የገነቡት ሁሉ ፈርሷል። “አል ጀምሃሪያ” ወይም “የህዝብ አስተዳደር” ይሉት የነበረው የአገዛዝ መዋቅር ተንዷል። የጋዳፊው “የአብዮታዊ ዲሞክራሲ” መጽሃፍ ማለትም “አረንጓዴው መጽሃፍ” በአደባባይ ተቃጥሏል። በውጭ አገራት በጥሬ ገንዘብና በኢንቬስትመንት መልክ ያስቀመጡት በ120 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር የሚገመት ሃብት እንዳይንቀሳቀስ ተደርጓል። ጋዳፊ ያወደሱት ሁሉ ረክሷል። ጋዳፊ የሰቀሉት ባንዲራ ወርዶ፤ በእሳት ተማግዷል።

ከአርባ ሁለት ዓመታት አገዛዝ በኋላ ሊቢያ እንደገና እንደ አዲስ ሃገር ነፃነቷን አውጃለች። ሊቢያውያን ገና ብዙ ፈተናዎች ይጠብቋቸዋል፤ ቢሆንም ግን የችግሮቻቸውን ሰንኮፍ ነቅለዋል። ለዚህም ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ሊቢያዊያንን “እንኳን ደስ ያላችሁ!” ይላል።

መለስ ዜናዊ ከጋዳፊ ውድቀት ቢማር ለራሱም፣ ለቤተሰቦቹም፣ ለዘመዶቹም ምንኛ በበጀ! መለስ ዜናዊ ሆይ! በውሸትና በጉልበት የቆመ ሥርዓት እንዲህ በጥቂት ወራት ውስጥ ይደረመሳል። በውሸት እና በጉልበት የቆመ ሥርዓት ሲደረመስ ተጠርጎ ከሚጣል ፍርሽራሽ ውጭ ቀሪ ነገር አይኖረውም። ይህንን የምንለው በንድፈ ሃሳብ ደረጃ አይደለም፤ አንተም እኛም በዓይኖቻችን እያየነው ነው።

ግንቦት 7፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ሊቢያ ላይ እንደረሰው ዓይነት የህይወትና የንብረት መስዋዕትነት ሳይከፈል የሥርዓት ለውጥ ማምጣት ይቻላል ብሎ ያምናል። ለዚህ ግን የመለስ ዜናዊና ዘረኛ ቡድኑን ፈቃደኝነት ይጠይቃል። ስለሆነም በመለስ ዜናዊ ዙርያ ያላችሁ ሁሉ ወደ ልቦናችሁ ተመለሱ እንላለን። እብሪት የትም እንደማያደርስ ከጋዳፊ አይተነዋል።

በጋዳፊ ላይ የደረሰው ሁሉ ለመለስና ዘረኛ ቡድኑ ማስጠንቀቂያ ሊሆነው ይገባል። እኛ ነፃነታችንን እናከብራለን፤ እንወዳለን። እኛም እንደ ሊቢያውያን ለነፃነታችን የህይወት ዋጋ ጭምር ለመክፈል ዝግጁዎች ነን። ቆርጠናል፤ አምርረናል። መጨረሻችሁን ማሳመር ወይም ማበላሸት የእናንተ ምርጫ ነው።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!**

................................................................................................................................................

## አሸባሪውና ኢህአዴግ መራሹ ዘረኛ የወያኔ አገዛዝ በተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲ አመራር አካላትና አባላት ላይ እያደረሰ ያለውን ወከባ አጠናክሮ መቀጠሉ ተዘገበ

ኢትዮጵያዊያንን በጠመንጃ ሃይል ረግጦና በስልጣን ወምበር ላይ ተፈናጥጦ ለዘመናት መቆየት የሚፈልገው ዘረኛ የወያኔ አገዛዝ እድሜየን ያሳጥራሉ ብሎ የፈራቸውን የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ አመራር አካላት፣ አባላት፣ አክቲቪስቶችና ጋዜጠኞች ሽብርተኞች ናችሁ የሚል ታፔላ እየለጠፈ ወደ ቃሊቲ እስር ቤት በግፍ ሲያጉር እንደቆየ የሚታወቅ ሲሆን ይህኑ ተግባሩን በማስፋፋት፣ በመድረክ አባላት ላይ የሚያደርገውን ማሳደድ አጠናክሮ መቀጠሉ ተዘገበ።

የኢትትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት የደረሰው መረጃ ዋቢ በማድረግ እንደዘገበው፣ ኢህአዴግ መራሹ ዘራፊ የወያኔ አገዛዝ የአረና ትግራይ አባል የሆነው አማረ ተወልደ በሁመራ አካባቢ የድርጅቱን ወረቀት ሲበትን ተገኝቷል በሚል ሰበብ ለበርካታ ቀናት በቁጥጥር ስር ካዋለ በሁዋላ በመጨረሻም ንብረቱንና እቃዎቹን ተቀምቶ በሳምንቱ መጨረሳ መለቀቁን ገልጹአል። በተመሳሳይ ዜና የዚሁ የአረና ትግራይ አባል የሆኑት አቶ አያሌው በዬነ በሽሬ ከተማ የፓርቲውን ወረቀት ሲበትኑ ተገኝተዋል በሚል ሰበብ በቁጥጥር ስር መዋላቸውም የታወቀ ሲሆን መምህር ጎይቶም ጺጋየ የተባሉት ደግሞ የተቃዋሚ ፓርቲ አባል ናቸው ተብለው ከስራቸው እንዲባረሩ መደረጋቸው ተገልጹአል።

ባለፈው ሳምንት ፋሽስቱ መለስ ዜናዊ የወያኔ ስብስብ በሆነው ፓርላማ ውስጥ ተገኝቶ ባደረገው ንግግር የመድረክ በርካታ አመራሮች የአሸባሪ ድርጅት አባላት ናቸው ማለቱን ተከትሎ፣ ለሆዳቸው ያደሩ ካድሬዎች በመድረክ አባላት ላይ የሚያደርሱትን ወከባ አጠናክረው መቀጠላቸው ተዘግቦአል። አቶ አያል ጌታነህ የተባሉ በምስራቅ ጎጃም የሚኖሩ የአንድነት ፓርቲ አባልም እንዲሁ ከማንኛውም ማህበራዊ ግንኙነት ለአንድ አመት ታግደው እንዲቆዩ የወረዳው ፍርድ ቤት የወሰነባቸው መሆኑም ታውቁአል።

በተመሳሳይም መልኩ በዚሁ ዞን ውስጥ የሚኖሩት አቶ ሀብታሙ አያሌውና አቶ ዘመድያ አገዘ የተባሉት የፓርቲው አባሎች ካለፈው አንድ ወር ጀምሮ የደረሱበት ያልታወቀ ሲሆን አቶ ሻምበል የሽዋስ ይሁን የተባሉ የምእራብ ጎጃም ነዋሪም ካለፉት ሶስት ሳምንታት ጀመሮ አድራሻቸው መጥፋቱን ለኢሳት የደረሰው መረጃ ያመለከተ ሲሆን፣ መምህር ሙሳ ኢብራሂም የተባሉ የዚሁ ፓርቲ አባልም በድብደባ ህይወታቸው ማለፉ ታውቁአል።

ስልጣንን ያለማንም ተቀናቃኝ የሙጥኝ ያለው የዘረኛና አምባገነኑ መለስ አገዛዝ ከፍተኛ ስጋት እየሆነ የመጣውን ህዝባዊ እንቅስቃሴ ለማፈን እንደመድረክ ባሉ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ አመራር አካላትና አባላይት ላይ ሰፊ ዘመቻ የጀመረ ሲሆን አንዱአለም አራጌ፣ አልባና ሌሊሳና በቀለ ነገአን የመሳሰሉት የመድረክ አመራሮች በአሸባሪነት ስም ለእስር መዳረጋቸው ይታወሳል።

## ኢትዮጵያ ሶማሊያን በመዉረር አልሼባብን አጠናክራለች ሲሉ አንድ ብሪታኒያዊ ተመራማሪ ገለጹ

በብሪታኒያ ጥልቅ የፖለቲካ የምክክር መድረክ የሆነዉ ቻታም ሃዉስ የአፍሪቃ ፕሮግራም አማካሪና ተመራማሪ ሮጀር ሚድልተን ኢትዮጵያ ሶማሊያን በመዉረር አልሼባብን አጠናክራለች ሲሉ ገለጹ። ተመራማሪው ይህንን የገለፁት ባለፉት አምስት ቀናት ዉስጥ የኬንያ ወታደሮች በሶማሊያ ዉስጥ ጣልቃ መግባታቸዉን በማስመልከት በሰነዘሩት አስተያየት ነዉ።

ሮጀር ሚድልተን ይህን መሰል ያልታሰበበትና አሉታዊ የሆነ ጣልቃ ገብነት የሚያስከትለዉን ዉጤት ካለፈዉ የኢትዮጵያ ወረራ ያለመማር ስህተት እንደሆን በመግለፅ ፣ በ2006 የተደረገዉ የኢትዮጵያ ወረራ የብዙዎች ጥምረት የነበረዉንና ህዝብ የተቀበለዉን የእስልምና ፍርድ ቤቶች ምክር ቤትን በማፍረስ ብቻዉን የቆመ፤ ብዙ አካባቢዎችን የተቆጣጠረ አክራሪ ሃይል የሆነዉን አልሸባብን የፈጠረ መሆኑን ጠቅሰዋል።

በተባበሩት መንግስታት ድርጅት፤ በዩናይትድ ስቴትስ መንግስትና በኢህ አዴግ መራሹ የወያኔ አገዛዝ በ2006 በሶማሊያ ዉስጥ የተደረጉት ወታደራዊ ጣልቃ ገብነቶች በጠቅላላዉ በአካባቢዉ የነበረዉን ሁኔታ ከማሻሻል ይልቅ ለእራሳቸዉም አገር ሆነ ለሶማሊያ ህዝብ ይበልጥ መጥፎ ችግርችን የፈጠሩ መሆናቸዉን ሮጀር ሚድልተን መግለፃቸዉን አል አፍሪካን ኒዉስ አመልክቷል።

የዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ቁንጮ መለስ ዜናዊ በራሱ ውሳኔ በሶማሊያ ላይ ወረራ እንዲፈጸም ሲያደርግ እጅግ በርካታ ኢትዮጵያዊያን ምሁራን፣ በወቅቱ በነበረው ፓርላማ መቀመጫ የነበራቸው ተቃዋሚ ፓርቲ ተመራጮችና ሰፊው ህዝባችን ድርጊቱን በጥብቅ አውግዘው እንደነበር የሚታወስ ሲሆን በወያኔ ጣልቃገብነት የተቆጣው የሱማሊያ ህዝብ ሆ ብሎ በመውጣት ወያኔ ያሰማራውን የኢትዮጵያ ጦር እንደወጋና የሞቱትን ዜጎች አስከሬን ጎዳና ለጎዳና በመጎተት ነዳጅ እያርከፈከፈ ሲያቃጥል በርካታ የአለም ዜና አውታሮች በምስል በተደገፈ ዘገባ ሲዘግቡት እንደነበር ይታወቃል።

## መለስ ዜናዊ ብሄራዊ ስሜት የለውም!!!

ከሰሞኑ የመለስ ካድሬዎች አንድ ሙግት ይዘዋል። እንደ መለስ ያለ ብሄራዊ ስሜት ያለው መሪ በኢትዮጵያ አልተነሳም የሚል። መለስ ለአሜሪካና ለአውሮፓ መንግስታት ከሚያጎበድዱ ሞታቸውን ይመርጣሉ ብለውም ያሞካሿቸዋል። ይሄንንም እውነት ነው ብለን እንድንቀበለው ይገፋፉናል።

መለስ ዜናዊ ያን አሳፋሪ ተክለ ሰውነቱን እንዲገነቡለት አይጋ ፎረም የተባለውን ድህረ ገጽ አቋቁሞና ነውረኛ ግለሰቦችን ቀጥሮ ነጋሪት እያስጎሰመ ነው። የአይጋ ፎረምና የእድምተኞቹ ከንቱ ጩኸት የአገሪቷን ገንዘብ ከማባከን በስተቀር ለኢትዮጵያችን ያተረፈው በጎ ነገር የለም።

መለስ ዜናዊ ብሄራዊ ስሜት የለውም። ብሄራዊ ስሜት ያለው ሰው ቢሆን ኖሮ ብሄራዊ ማንነቱን ከክልላዊ ማንነቱ አግዝፎ የአገርን አንድነት የሚሸረሽር ተግባራትን ባልፈጸመ ነበር። “ወርቅ ከሆነው ዘር በመወለዴ ኩራት ይሰማኛል” በማለት |ሌሎቻችንን ከመዳብ ወይም ከከሰል ከየትኛው እንደመደበን እርሱ ብቻ ያውቃል| ባልተመጻደቀ ነበር።

መለስ ዜናዊ ብሄራዊ ስሜት ቢኖረው በዜጎች መካከል ያለውን ልዩነት ህዝቡን ለመከፋፈልና ለማዳከም አይጠቀምበትም ነበር። መለስ ዜናዊ ብሄራዊ ስሜት ስለሌለው ዜጎችን በጎሳቸው ይከፋፍላል። አንዱም ጎሳ የአንዱ ጠላት እንደሆነ አድርጎ ይሰብካል። በህወሃት ማንፌስቶ ላይ የትግራይ ህዝብ ቀንደኛ ጠላቶች “አማራና ኤምፔሪያልዝም” ናቸው ተብሎ የተጻፈው የመለስን ብሄራዊ ስሜት ማጣት አመላካች ነው።ይህ ግለሰብ በኦሮሞዎችና በአማሮች መካከል ሊፈጥር የሞከረው እልቂትም የሚረሳ አይደለም።

መለስ ዜናዊ ብሄራዊ ስሜት ቢኖረው ዜጎች ዘመኑ የደረሰበትን ሁኔታ ለማወቅ የሚያስችላቸውን የመገናኛ ብዙሃን እንዳያገኙ ሬዲዮኖችን፤ ቴሌቭዥኖችን፤ ልዩ ልዩ ድህረ ገጾችንና፤ ጋዜጦችን ማፈን ባላስፈለገው ነበር።መለስ ዜናዊ ብሄራዊ ስሜት ስሌለው በአገሪቷ ውስጥ ነጻ አስተሳሰብ እንዳይሰፍን ዜጎችን አስሮ ይዟል። ዜጎች ከመረጃ ርቀው በጨለማ ውስጥ እንዲኖሩ ለማድረግ ብዙ ገንዘብ ከአገሪቷ ካዝና እያወጣ ለቻይናና ለሌሎች ይበትናል። እንዲህ ያለ ግለሰብ ብሄራዊ ስሜት አለው ለማለት አይቻልም።

መለስ ዜናዊ ብሄራዊ ስሜት ቢኖረው በብዙዎች ደምና አጥንት የቆመችን ባንዲራ የጨው መጠቅለያ ጨርቅ ነው ብሎ ባልተሳደበ ነበር። ኢትዮጵያዊያኖች “ወድቃ በተነሳችሁ ባንዲራ” ሲባሉ ከቆሙበት ሳይንቀሳቀሱ ለባንዲራቸው ያላቸውን ክብር ሲያሳዩ ኑረዋል። ዜጎች የሚኮሩበትንና የሚመኩበትን ደግ ነገር ሁሉ ማንቋሸሽና ማዋረድ መለስ ዜናዊ ተልእኮው ነውና ባንዲራን ጨርቅ ቢል ብዙም አንደነቅም። እንዲህ ያለ ግለሰብ ብሄራዊ ስሜት አለው ተብሎ ሲሰበክለት ግን ያሳፍራል።

በዓለማችን ላይ አሉ የሚባሉ ድሃ አገሮች ልጆቻችንን ለአረቦች አሳልፈን አንሰጥም ሲሉ መለስ ዜናዊ ግን ኢትዮጵያዊያን ወጣት ሴት ልጆችን ለአረቦች አሳልፎ በመሸጥ ጉድ ያሰኘ ተግባር ፈጽሟል።ወጣት ሴቶችን በራሱ ሰዎች አማካኝነት ባቋቋመው ድርጅት አማካኝነት እየሸጠ ብዙ ገቢ ማግኛ መንገድ አድርጎት ቆይቷል። ዜጎቻቸውን ወክለው በዓረቡ ዓለም የተቋቋሙ ኤምባሲዎችና ቆንሲላዎች የሴቶቻችንን መከራና ስቃይ ለመታደግ ምንም ዓይነት ጥረት አለማድረጋቸው የመለስ ዜናዊን ብሄራዊ ስሜት ማጣት ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ድርጊት ነው።

ብሄራዊ ስሜት ያለው መሪ ከአገሩ ዜጎቹ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ህዝብ ለዕለት ጉርሱ ከፈረንጅ አገር በሚመጸወት የእርዳታ ስንዴ ላይ እየተማመነ ከ8 ነጥብ 6 በላይ የአሜሪካን ዶላር ገንዘብ ሰርቆ በባዕድ አገር ባንኮች አያከማችም። መለስ ዜናዊ ግን ኢትዮጵያ ለምትባል አገር በጎ ስሜት ስለሌለው የዝርፊያው ቀንደኛ መሪ በመሆን አገሪቷን የዘራፊዎችና የወሮበላዎች መናኸሪይ በማድረግ ለኢትዮጵያችን ያለውን ክፍ ስሜት አሳይቶናል።

ብሄራዊ ስሜት ያለው መሪ የገዛ አገሩን ድሃ ገበሬዎች አፈናቅሎና መሬት አልባ አድርጎ ለኢትዮጵያ በጎ አመለካከት ለሌላቸው ቡድኖች ለምና ድንግል መሬቶችን በመሸጥ ዜጎችን የባእዳን ጥገኛ አያደርግም ነበር።መለስ ግን መሬቱን ለተቀራማቾች በማከፋፈል ኢትዮጵያዊያንን ያሳዘነ ተግባር ፈጽሞ ብሄራዊ ስሜት የሚባል ነገር እንደሌለው ያስመሰከረ የኢትዮጵያችን ጠላት የሆነ ግለሰብ ነው እንጂ ብሄራዊ ስሜት አለው ተብሎ መወድስ ሊቀርብለት የሚገባ ግለሰብ አይደለም።

እኛ ኢትዮጵያዊያን መለስ ዜናዊን የምናውቀው በአገር ከዳተኝነቱ ነው እንጂ በብሄራዊ ስሜቱ አይደለም። እርሱን የምናውቀው ባየነው ተግባሩ ነው እንጂ በነውረኛ ቡድኖች ሊገነባለት የሚሞከረውን ተክለሰውነት አይደለም። ይህን አገር ከዳተኛና ዘረኛ ግለሰብ ከጫንቃችን ላይ አሽቀንጥረን ወዲያ መጣል የኢትዮጵያዊነት ግዴታችን ነው። መለስና ዘራፊ ቡድኑን ከተቆናጠጡበት ስልጣን ላይ አውርደን ለመጣል ሳናቅማማ የሚፈነቀሉ ድንጋዮችን ሁሉ እንፈነቅላለን።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

## የፋሽስቱ መለስ ዜናዊ ውድቀት እንደሊቢያው ሙአመር ጋዳፊ ... (ከገጽ 1 የዞረ)

ይሰጣል ያሉት እኒሁ የፖለቲካል ሳይንስ ምሁር እነመለስ ዜናዊ ይህን ክስተት ቆም ብለው ሊያስተውሉና ሳይጨልምባቸውም ማስተካከል የሚገባቸውን ሁሉ ቢያስተካክሉ ይሻላቸዋል ብለዋል። በመጨረሻም፣ በተለያዩ አፋኝ ዘዴዎችና የጭካኔ ርምጃዎች ህዝብን ረግጦ ለረጂም አመታት መግዛት ያለፈበት የቁማር ጨዋታ በመሆኑ ራሳቸውን የማስተካከያ ጊዜው ካለፈ በሁአላ ሊከተል የሚችለው ውድቀት እንዲህ በቀላሉ መግለጽ የሚቻል አይደለም፣ እናም ለሁላችንም የሚበጀውን ነገር ነገ ዛሬ ሳይሉ ማስተካከያ ያብጁለት ዘንድ እመክራቸዋለሁ በማለት አስተያየታቸውን አጠቃለዋል።

ሙአመር ጋዳፍ የተቃዋሞዎቻቸው እየተጠናከሩ መምጣት ተመልከተው እራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ከእንዲዚህ አይነት የውረደት ሞት የማዳን ሰፊ እድል የነበራቸው ቢሆንም በታሪክ ተደጋግሞ ከታየው የአምባገነኖች ፍጻሜ እጅግ ዝቅ ባለ ውርደት አይጦች በሚርመሰመሱበት የቆሻሻ ማስተላለፊያ ቱቡ ውስጥ እስከመደበቅ ደርሰው የፍጻመውን ሞት የሞቱ መሆናቸው ብዙዎችን አስገርሞአል።

መለስ ዜናዊና ግብረአበሮቹ እንደ ሊቢያው መሪ ህዝብ ሳያስጨርሱ መጨረሻቸውን ለማሳመር ያላቸው ጊዜና ተስፋ ከ እጃቸው እያመለጠ መሆኑን የግንቦት 7 ንቅናቄ ደጋግሞ እየገለጸ ይገኛል።

## በሃዲያ ዞን የሚገኙ የሶስት ወረዳ ህዝቦች ለጥያቄአቸው ምላሽ ካላገኙ ... (ከገጽ 1 የዞረ)

በኢትዮጵያ ውስጥ በህዝቦች መካከል ለረጅም ዘመናት አብሮ የቆየው አንድነትና መተሳሰብ እሴት በተለይም የዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የስልጣን ወምበርን ከተቆናጠጠ ወዲህ እየጠፋ፣ የኢትዮጵያ አንድነት ከመቼውም ጊዜ በበለጠ እየተዳከመ መምጣቱን በርካታ ምሁራን ሲገልጹ የቆዩ ከመሆኑም በላይ የድህነቱ መባባስና ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የሚከተለው የብሄር ፖለቲካ ለዚህ አስተዋጽኦ ማድረጉም በተደጋጋሚ ስንገልጽ መቆየታችን የሚታወስ ነው።

ይህ በዚህ እንዳለ በዚሁ በደቡብ ክልል ዳውሮ ዞን እየተባለ በሚጠራው አካባቢ የሚገኝ የዋካ ከተማና አካባቢ ህዝብ የጀመረው የተቃውሞ አመጽ በተጠናከረ መልኩ የቀጠለ ሲሆን በተለይም ማክሰኞ እለት የተነሳው ተቃውሞ ሌሊቱን በሙሉ አድሮ በማግስቱም ተጠናክሮ መቀጠሉን ከስፍራው ዘጋቢያችን በላከልን መረጃ አመልክቷል።

እንደ ዘጋቢያችን ሪፖርት የአካባቢው እና የክልሉ ፖሊስ ሁኔታውን መቆጣጠር ባለመቻላቸው በ7 መኪና የተጫኑ የፌደራል ፖሊስ አባላት እንዲሁም የዘረኛው አገዛዝ የክልሉና የፌደራል ባለስልጣናትም በአካባቢው መገኘታቸው ታውቁአል። ከዚሁ የተቃውሞ አመጽ ጋር በተያያዘ እስካሁን ድረስ ከ26 ያላነሱ ሰዎች ተይዘው መታሰራቸውንና 4 ግለሰቦች ደግሞ ከፉኛ ተደብድበው መታሰራቸውን ለማወቅ ተችሎአል።

እንደዘጋቢያችን ሪፖርት ከተሳሩት መካከል አቶ አድነው ማሞ፣ ተፈራ ታደሰ ፣ ምትኩ በቀለ፣ ከበደ ኮኑ፣ ግርማ ጌታቸው ፣ ካሰች ተገኝ፣ አብነት አግደው፣ዘነበ ገርገራ፣ ጥረቱ ሀይሌ እንደሚገኙበት የታወቀ ሲሆን ከተለያዩ ቀበሌዎች እየተመመ ወደ ከተማው የጎረፈው ህዝብ የታሰሩት ተወካዮቻችን ካልተፈቱ በስተቀር ተቃውሞአችንን እንቀጥላለን ማለቱን ዘጋቢያችን ያነጋገራቸው የአካባቢው ተወላጆች ገልጸዋል።

በሌላም በኩል ከዚሁ ህዝባዊ አመጽ ጋር በተያያዘ ትምህርት ቤቶችና ሌሎች ማህበራዊ አግልግሎት የሚሰጡ ተቋማት በሙሉ የተዘጉ ሲሆን፣ የአካባቢው ነዋሪዎችም " ዳውሮ ላይ የመንግስት ስርአት የለም፣ ልማት የለም፣ እስራትና ድብደባ ይቁም፣ የሚሉ መፈክሮችንና "ነጻነት አጣን እኛ የዋካ ልጆች፣ ስርአቱ ገደለን የዋካን ልጆች" የሚል ይዘት ያለው መዝሙር ሲዘምሩ መሰማታቸውን የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት ዘግቡአል።

## “የምክር ቤት አባልነቴ፤ በቴሌቪዥን ቢሆንልኝ ይሻል ነበር” ሲሉ ... (ከገጽ 1 የዞረ)

አያይዘውም በተቃራኒው ግን የወያኔው አገዛዝ ጋዜጠኞች የነዚህ ሰዎች ጉዳይ በፍ/ቤት ሳይረጋገጥ ወንጀለኛ ናቸው ሲሉ ይፈርጇቸዋል። ስለዚህ ‹ጋጠ-ወጥ› መባል ያለባቸው የአገዛዙ ጋዜጠኞች እያሉ፤ ሰዎችን ነፃ ብለው የሚያስቡትን ‹ጋጠ-ወጥ› ማለት ግን ተገቢ አይመስለኝም”ብለዋል። ዘረኛው መለስ ፍርድ ቤት ገና ጥፋተኛታቸውን ሳያረገግጥባቸው ሰዎች “ነፃ ናቸው” ብለው እየፃፉ ነው ያሏቸውን ጋዜጠኞች “ጋጠ-ወጥ” ካሏቸው፤ በዚያው መድረክ ላይ :-”የታሰሩት ወንጀለኞች ናቸው። አንድም ሰው ያለ ማስረጃ አልታሰረም። ለሁሉም በቂ ማስረጃ አለ” እያለ ዳኛ ሆኖ ፍርድ ሲሰጥና ተፅዕኖ ሲፈጥር የነበረው ራሱ መለስ ምን ይሆን የሚባለው? በማለት ታዛቢዎች መጠየቃቸውን ኢሳት ዘግቡአል።

## የእኛኑ ገሀነብ ማን እንዲያፈርስልን?

እፉኝ ነኝ እንዴ
ወፍ ዘራሽ መደዴ
በንፋስ አቅጣጫ ሚወሰን መንገዴ።

ብናኝ አቧራ ነኝ? ከጠጠር የከሳ
እፍ ባሉት ቁጥር በኖ የሚነሳ ።

ቆሻሻ ነኝ እንዴ? የምድር ላይ ጥራጊ
ከግም ከብስብሱ አንድ ላይ ታሻጊ።

አረም ነኝ ወይ እንዴ? ተመዝዤ እምጣል
የማበብ መብት ያጣሁ ከፍጥረታት መሃከል።

እንዴት ልገልጸው ነው ሰውነት የኔን
የክብር አቅል አጥቶ የቀለለውን
መያዣው ጠፍቶበት እሚባክነውን
ንቀሉኝ፣ ጥረጉኝ፣ እፍ በሉኝ ብሎ እጅ የሰጠውን።

በፈጣሪ ምስል ሁሉን ተከሽኖ
በአንድየው ሲቀመር ፍጥረት በእኩል ገኖ
ድንገት ሽርተት ብሎ፣ አንዱ አሳሪ ሆኖ የቀረው ታሳሪ
አንዱ ተለጉሞ ሌላው ተናጋሪ
ምንድነው ታምሩ? ያንዱ ሆዱ ሞልቶ ላይ ታቹ ሲያፈስ
አዋይ በሌላው ቤት ቦዶ ሌማት አቅፉ አምራ ምታለቅስ
አንዱ የመነመነ፣ በረሃብ ዋግምቶች ደሙ የተበጣ
ሌላው ጥጋብ ነፍቶት የሚሰራው ያጣ።

አንዱ አገር አልባ የስደት ምርኮኛ
ሌላው ሳር ቅጠሉን፣ ምድርና ሰማዩን አቅፎ የሚተኛ
የከርሰ ምድሩ ሃብት፣ የወንዝ ሽንተረሩ፣ ባለቤት ቀማኛ
በእጽዋት በንስሳው፣ በሰው በፍጥረታት ላይ ፈላጭ
ቆራጭ ዳኛ።

ምንድነው ሚስጥሩ አንዱ ሃር ለባሽ
ባልማዝ በፈርጥ አጊያጭ በሽቶ ተንበሸባሽ
ደረቱን ገልብጦ ባለም ፊት ጋላቢ
ሌላው አንገት ደፊ፣ አሮጌ ነጠላ በእድፍ ላይ ደራቢ
ጠኔ እግር ነስቶት በደረት ተሳቢ
መዋያው ማደሪያው ከግማት ከእጣቢ።

ማነው ያመቻቸው እንዲህ አይነቱን ብልጠት
ለማሳኝ መከራን ለዘራፊ ግነት
ብትውቱን ከታች፣ ከላይ እብሪተኛን
ተንኮልን ከፍ ከፍ፣ ቁልቁል ንጽህናን
ለከሃዲ ሙልሙል፣ ለታማኝ ቅጥቃጭ
ጥቂቱ ተኮፋሽ፣ ብዙሃን ተረጋጭ።

ከቶ ማንን ይሆን የምናማርረው
ፈጣሪን እንዳንል፣ ይህ ክስ የሃሰት ነው
ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ ህሊና እማይፈቅደው።

በአምሳሉ ፈጥሮናል ብለን ተተብተን
እንኳን የሱን ክፋይ፣ ሰው መሆን ሲያቅተን
በገዛ ስራችን በየብጤታችን ባመጣነው ጣጣ
ሌባ ጣት ብንቀስር፣ የግዜር አይን እስቲወጣ
ማምለጫ የለውም ማን እንደሚጠየቅ
ለወደቅንበቱ የስቃይ የንግልት የውርደት መቀመቅ።

ያገር ውስጥ ገሃነብ የገነባን እኛ።
እሳት የሚጠብሳት ነፍሳችንም የእኛ።
መውጫን የዘጋነው ሰይጣኖቹም እኛ።

ሾፐንሃወር በሚባለው የጀርመን ፈላስፋ አባባል ኩርኮራ
የተጻፈ

**ቱፋ ጥቅምት 2003**

## ይድርስ ግንቦት ሰባት ይድረስ

እናት ዓለም ግንቦት ሰባት፣ ተራሮችሽ ተሰለፉ!
ግንቦት ሃያን አሳፈሩ! በድል ድባብ ተንሳፈፉ
የጥላቻን ዓይን ጥላ፣ በአንድነታቸው ገፈፉ
ትውልድሽ እምቦቀቅላሽ፣ በአገር ፍቅር ተቃቀፉ
የኢትዮጵያዊነትን ማተብ፣ በቁርጥ ቃል አበሰሩ
የምስራች ተቀዳጁ! የምስራች ተባበሩ።

እናት ዓለም ግንቦት ሰባት፣ ትውልድሽ ቆሞ በፅናት
መሰከሩ ሰማዕታት፣
የልጆችሽን ትንሳኤ፣ ከአፅናፍ አፅናፍ ፀሃይ ሞቀው
ዓለም አየው! ጠላት ለየው!
የአባቶቹ ወኔ ደሙን፣ ኢትዮጵያዊነቱን ጫረው
ማንም ሰው ሳያስገድደው፣ ህዝባዊነቱን ገለፀው
ማንነቱን መሰከረው

ሣር ቅጠሉን አለበሰው፣ አደባባዩን ሸፈነው
ሰማዩን አጥለቀለቀው፣ ዓለምን አስጠነቀረው፤
እሰይ! እሰይ! ሞት ፍርሃት! እሰይ! እሰይ! በራ ንጋት
የምስራች የኢትዮጵያ ሕዝብ! ክብሩ ሞቱ ለሰማእታት!
በድባብ ሂጅ የኢትይጵያ እናት፤ ክብርህ ይስፋ የኢትዮጵያ አባት
ተባረክ የኢዮጵያ ወጣት፤ተመንደግ የኢትዮጵያ ህፃናት!
እንኳን! እንኳን የኢትዮጵያ አምላክ፣ አበቃን ለድል ብስራት!

ሕዝብ ሆይ ከግንቦት ስምንት፣ የባንዶች አዋጅ ተጠንቀቅ
በምርጫህ በድምፅህ ትግል፣ የያዝካትን ድል አትልቀቅ!

የሕዝባዊ ሥልጣንክን ግብ፣ የዴሞክራሲህን ብቅል
በአዋጅና በጠመንጃ፣ በማስፈራራት እንዳትጥል!
ይልቅንስ ሰልፍህን ቀጥል!
ባለቤቱ አንተ ነህና፣ ለባንዲራውም ለአገሩም
በሰልፍህ ላይ ዳግም ዘብ ቁም!
የህዝብ ሰልፍ! የህዝብ ቃል!
እንኳንስ የባንዳን አዋጅ፣ ተራሮችን ያነቃንቃል።
ሰማይ ምድር ያናውጣል።

የምስራች የኢትዮጵያ ሕዝብ! እልል! እልል! እልል! እልል!
ከእንግዲህ አንኳንስ አዋጅ፣ እንኳንስ የታንክ ቁልል
እንኳንስ የድምፅ ሌባ፣ እንኳንስ የእስታሊን ቅጥል
ማንም ሃያል አይገድብህም፣ ባንድ ሽ ጊዜ ቢፏልል፣
በሰላም ጥሰሃልና፣ የምዕራፍ አንድን እክል
በመንፈስ ታጥቀሃልና፣ ለምዕራፍ ሁለት ድል
ማንም ሃይል አይገድብህም፣ መለስ የሞት ጣር ቢያቃጭል
እንኳንስ አዋጅ! ኡኡ! ቢል!...

ይድረስ ግንቦት ሰባት ይድረስ! በሕዝባችን ቆራጥ መንፈስ!
ዘረኛው ጎጥ አይኑ እስኪፈርስ!
የሠልፍ ድል ይንቀሳቀስ።

አዲስ አበባን ከአደጋ፣ ኢትዮጵያን ከጎጥ መንጋጋ
መንጭቆ ከጅብ አፍ ስጋ
ያወጣትን የሕዝብ ሠልፍ
መለስ በጠመንጃ እንዳይጠልፍ፣
የሰልፍ ድል ይንቀሳቀስ።

የምርጫ ሳጥን እንደ አይጥ፣ ቦርቡሮ እንዳይጨርስ በውስጥ
ጊዜ ገዝቶ በድለላ፣ ተቃዋሚውን እንዳይለውጥ፣
የሰልፍ ድል ይንቀሳቀስ።

የተቃማዊዎች ወገን፣ ተደጋግፈህ ተዋህደህ
እንደ አንድ አካል ፀንተህ ቆመህ፣
የሰልፍ ድል ይንቀሳቀስ።

ፅና! ተቃዋሚ ፅና! በሕዝባዊ ቃልህ ሚና፣
ሕብረቱ ከትግራይ ምርጫ፣ ሲባረር በአፈሙዝ ጫና
ያለአንዳች ተወዳዳሪ፣ ዓድዋ ላይ መለስ ሲቅናና
የትግራይ ወጣት ውርደቱን፣ አልቀበል ብሎ በቁርጥ
ድረስልኝ ሲልህ በግልጥ

ምርጫው በሰላም ዳግመኛ፣ እንዲካሄድ እንደገና
የኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ፣ ጮሆ ጠይቆሃልና
ፅና! ተቃዋሚም ፅና! በህዝባዊ ቃልህ ሚና
ስበር የመለስን ጫና። ....

በራሱ ልሳን ነግረኸው፣ ካነቀው የራሱ ላንቃ
አትድከም ቋንቋ ሽምቀቃ
ንገረው በጭራቁ ቋንቋ፣ ንገረው በአባትህ ቋንቋ
ምከረው በአፋር በኢሣ፣ ድገመው በወላኢታ
ሰልሰው በኦሮሚፋ፣ አጥምቀው በኩሎ ኮንታ
አላ ሙድን እስኪረት! ካርተር ውሸቱ እስኪገታ!

ወያኔ ነፃ እስኪወጣ፣ ከዘረኝነተ እመቃ
ንገረው በአባትህ ቋንቋ። ንገረው በእናትህ ቋንቋ። ....

በዘውድም ሆነ በደርጉ፣ ዛሬም በወያኔው አገር
ሰምተነው አናውቅም ሕዝቡን፣ በአባቱ ቃል ሲነጋገር፣
ነፃ አወጣንህ እያልነው፣ ድምፁን ከመሸምቀቅ በቀር።

በአፍ ልማድ ማደንቆር ለምደን፣ ሥልጣን የህዝብ ነው ብለን
ዋሽተን በብልጠት ሕዝቡን ሸንግለን
ለጎምነው እንጅ ልሳኑን፣ አልሰጠነውም ስልጣኑን
አልሰማነውም የአባቱን፣...

ፅና! ተቃዋሚ ፅና! በሕዝባዊ ቃልህ ሚና
ስበር የመለስ ጫና።

እናት አለም ግንቦት ሰባት፣ ተራሮችሽ ተሰለፉ
ግንቦት ሃያን አሳፈሩ፣ በድል ድባብ ተንሳፈፉ
የጥላቻ ዓይነ ጥላ፣ በአንድነታቸው ገፈፉ
ትውልድሽ እምቦቀቅላሽ፣ በአገር ፍቅር ተቃቀፉ
የኢትዮጵያዊነትን ማተብ፣ በቁርጥ ቃል አበሰሩ
የምስራች ተቀናጁ! የምስራች ተባበሩ።

**ከሎሬት ጸጋዬ ገብረመድን**
**በጦቢያ መጽሄት ቅጽ 12 ቁጥር 10 ግንቦት ወር 1997 ዓ.ም**
**ወጥቶ ከነበረ የተወሰደ**

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ**
**እንደሚከተለው ነው።**
መካከኛ ሞገድ:- በ 358 MB, በ 837 kHz
አጭር ሞገድ:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz
እና በ 60 MB 4760 GHz
ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡00 እስከ 2፡30 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን። ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**
ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org